# የተደበቁ እውነቶች!

## ኢትዮጵያን ሯጮች በሳውዲ የደገሙት የአረንጓዴው ጎርፍ ድል!

ክፍል 9

ነቢዩ ሲራክ- ከሳውዲ አረቢያ

ከሰሞኑ ሰበር ቅኝት . . .

ወደ እኛ ዘመን የተስፋ ምድር ወደሆኑት አረብ ሃገራት በተለይም ወደ ሳውዲ አረቢያ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሚያደርጉት ጉዞና በሚያጋጥማቸው መከራ ዙሪያ በተከታታይ ክፍሎች የማደርገውን ቅኝት አላቆምኩም። ያለፈውን በትዝታ የማስቃኘው ዝካሬየ ነገም ይቀጥላል. . . . የዛሬው ቅኝቴ ከዚህ በፊት እንደማደርገው በሰሞነኛው ትኩረቴ በጅዳው ማራቶን በኢትዮጵያን አትሌቶች በተገኘው ድል ዙሪያ በማተኮር ያየሁ የሰማሁትን ከመረጃ ጋር ላጋራችሁ ግድ ይለኛልና ፈቃዳችሁ ከሆነ ተከተሉኝ. . .




ተንቀሳሳሽ ስልኬ ደጋግማ ትጮሃለች . . . የተደወለልኝ ገጽታችን በስፖርት እንቀይር በሚል በአረብ ሀገራቱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በደግ የማይነሳ ስማችን ለመቀየር በሚደረግ የስፖርት እንቅስቃሴ ታች አምና የተዋወቅኩት ወጣት ነበር። ስማችንና ገጽታችን እንቀይር ብለው የተነሱት ወጣቶችን ዙሪያ አንድ ዘገባ ሰርቸ ነበር። ሁኔታውን ጠጋ ብሎ ለተመለከተው ሃቅ አለው ! አሁን አሁን በጥቂት ምግባረ ብልሹ ዜጎች በሚፈጸም ምግባር የብዙዎቻችን ስም በጥሩ አይነሳም። ገጽ ስማችን ለመቀየር ደግሞ ስፖርት ለጊዜው የተገኘው ብቸኛ አማርጭ በመሆኑን አጥብቀው ከሚያምኑት መካከል ይህ ወዳጅና ጓደኞቹ ዛሬ በጅዳ የሚደረገው ማራቶን የኢትዮጵያን አትሌቶች ተሳታፊ መሆን ልዩ ስሜት እንደሚሰጠው አያስተግርም። ስልክ የደወለለኝ ወዳጀ የሚሰራበት ኩባንያ የጅዳ ማራቶን ስፖንሰር ካደረጉት ኩባንያዎች መካከል አንዱ በመሆኑ አንዳንድ መረጃወችን ከሳምንት ጀምሮ ያቀብለኝ ነበርና የስልኩን ጥሪ እንደሰማሁ በማራቶኑ ዙሪያ ሊያነጋግረኝ እንደሆነ አልጠፋኝም። የሚንጫረረውን ስልክ ከማንሳቴ አስቀድሞ ፈጥኘ የተመለከትኩት የቀን መቁጠሪያየን ነበርና የስልኩን ጥሪ መልዕክት ለመገመት አልተቸገርኩም ። በአስገራሚ ፍጥነት ስለሚጓዘው ጊዜ ለማሰላሰልም ሆነ የጀመርኩትን ስራ ለመጨረስ ጊዜ አልዎሰድኩም። ስልኩን አንስቸ ወዳጀን አነጋገርኩት. . .ግምቴ ትክክል ነበር ! የጅዳው ማራቶች ለመጀመር ጥቂት ሰአታት እንደቀሩትና በውድድሩም ከሃገር ቤት የመጡ ታዋቂ አትሌቶች እንደሚሳተፉ ያልተጠበቀ አዲስ መረጃ አቀበለኝ ! ውድድሩ ከጥቂት ሰአታት በኋላ እንደሚጀመር ተጨዋውተን በውድድሩ ቦታ ለመገናኘት ቀጠሮ ይዘን ተለያየን። ስልኩን ከዘጋሁ በኋላ ከዚህ በፊት በዚሁ የጅዳ ማራቶን ሩጫ ተወዳድሮ የመኪና ሽልማት ወዳገኘው ወጣት ሙባረክ በመደጋገም ብደውልም ስልኩ አይሰራም። በኢትዮጵያ አለም አቀፍ ተማሪ የሆነው ሙባረክ ሩጫ በማይታሰብበት ሃገር ራሱን ጠቅሞ የሃገሩን ባንዴራ ከፍ አድርጎ እስከማውለብለብ ቢደርስም ይህን ወጣት በማበረታታቱ ረገድ ከትምህርት ቤቱ ጀምሮ የመንግስት ተወካዮችና በአካባቢው የምንኖረው ወገኖች ድጋፍ ስለልተደረገለት ብዙም ሊደርስ የሚችለውና ተስፋ የሚጣልበት ወጣት ብዙ መጓዝ እንዳልቻለ ራሴን ጭምር እየወቀስኩ ላፍታ ያህል አስታወስኩ !




ጉዞየን ወደ ማራቶኑ የውድድር ቦታ አደረግኩ . . . የቀይ ባህር ዳርቻ የሚገኘው አውራ ጎዳና አንድ የመተላለፊያ መስመር ተዘግቶ ዙሪያው ይጠበቃል. . . አልፎ አልፎ የመኪናና የእግረኛውን እንቅስቃሴው ለመቆጣጠር ይመስላል በርካታ የትራፊክ መኪኖቻቸውን ሰማርያዊና ቀይ መብራታቸውን እያንበገበጉ የሩጫውን መስመር ይቆጣጠራሉ። አልፎ አልፎ በመንገዱ ዳርና ዳር ውድድሩን ስፖንሰር ያደረጉ ኩባንያወች መለያ ባንዴራ ተንቀጠልጥሎ ይስተዋላል። ይህንን እየቃኘሁ የቀይ ባህርን ዳርቻ በመያዝ የውድድሩ መዳረሻ ወደ ሆነው አብሁር Red sea mall ቀይ ባህር ተብሎ ወደ ሚጠራው እጅግ ዘመናዊ የገበያ አዳራሽ አቀናሁ። ሰማዩ አይን ያዝ ማድረግ ይዟል። የሙቀቱ መጠን ወደ 36 ዲግሪ

ሴንቲግሬድ ዝቅ ብሏል፡፡ ከተንጣለለው የቀይ ባህር እየተነሳ የሚረጨው ወበቃማ ነፋሻ አየር ግን ሙቀቱ በረድ ያደረገው ይመስላል፡፡ ወበቁ ቢኖርም ሙቀቱ ብዙ አያቃጥልም፡፡ የቀኗ ጸሃይ ስራዋን ጨርሳ በቀይ ባህር ምዕራባዊ አድማስ በመጥለቅ ላይ ትገኛለች፡፡ የቀኑ ብርሃን ለጨለማ ቦታ መልቀቅ መጀመሩን ደንገዝገዝ



ያለውን ሰማይ ተመልክቶ መገመት ይቻላል ! . . . የውድድሩን መስመር ተከትየ ጉዞየን እንዳቀናሁ. . . በከፍተኛ የርቀት ልዩነት የተለያዩ ዜጎች በላብ ተጠምቀው እያለከለኩ ሲሮጡ አጋጠመኝ . . . የኢትዮጵያውያን ሯጮች ሽታ ግን የለም ! አልፎ አልፎ ቆም እያልኩ ፎቶ አነሳለሁ. . . ደግሞም አሻግሬ እመለከትና የምፈለገውና አጣለሁ ! የኢትዮጵያውያኑን ሯጮች ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ ያለኝ ጉጉት የምጨብጠው አሳጥቶኛል፡፡ የመድረስ አለመድረሳቸውን ሁኔታ ለማረጋገጥ ወደ ወዳጀ ደወልኩ፡፡ ውድድሩ ፍጻሜ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ይሆናል ተብሎ መገመቱን ሲነግረኝ አጭር አቋራጭን በመምረጥ ፍጥነቴን ጨምሬ ገሰገስኩ ! የተለያዩ ሀገር ሯጮች የሞት ሽረት የመጨረሻ ትግላቸውን ተፋጠው ሲዎዳደሩ ተመለከትኩ . . . ቀጫጭኑ ኢትዮጵያውያን ግን በትግሉ ውስጥ የሉበትም ! እነሱ ትግላቸውን የሚያካሂዱት እርስ በርሳቸው ነው ! ብዙም ሳይቆይ ከውድድሩ መጨረሻ የቅርብ ርቀት በሚገኘው ትልቅ የአለም ካርታ በሚታይበት አደባባይ ላይ ሆኘ ጥቂት መመልከት ብጀምርም የመግቢያ ሰአቱ እየተቃረበ በመምጣቱ የውድድሩን ፍጻሜ ለመመልከት ይቻለኝ ዘንድ ከገበያው አዳራሽ ግቢ በር ወደ ሚገኘው አውራ ጎዳና አቀናሁ፡፡ የትራፊኩን ግፊያ ተቋቁሜ በአብዛኛው አረብ ተመልካቾች መፈናፈኛ በጠፋበት ቦታ ተሹለክልኬ የውድድሩ መጨረሻ ፍጻሜ መድረክ አካባቢ ደረስኩ፡፡ ከወጣትና ጎልማሶች ሁሉም የዚህን ውድድር ፍጻሜ አሸናፊዎች ለማዎቅ ይንቆራጠጣል፡፡ አሸናፊው ከሃበሾች እንደማያልፍ ያጫዎተኝ ግን በዚህ ውድድር ላለፉት አመታት በማስተናገድ ስራ ላይ የተሰማራው ወጣት ሳውዲ ነበር፡፡ ምነው ብየ ጠየቅኩት" እንኳንስ ከሃገር ቤት መጥተው እዚሁ ያደገውን የሃበሻ ልጅ ማን ቻለው " ሲል የመለሰልኝ ኩራት ክብሩ አድምቆኝ ስሜቱ ከደሜ ሳይወጣ እኒያ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች መምጣጣቸው ተሰማ ! አካባቢው በጭብጨባና በጩኸት ተናጠ !

የዘንድሮው የጅዳ ማራቶች ይደረጋል ተብሎ መነገር ከጀመረ ከወር በላይ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮች ይህ መረጃ የላቸውም ማለት አይቻልም፡፡ ውድድሩ መኖሩን የሚያውቁትም ቢሆኑ በጅዳው



ማራቶች ከኢትዮጵያ ሯጮች የመምጣታቸው በቂ መረጃ ባለመኖሩም በጅዳና አካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎችን ትኩረት የሳበ አልነበረም ማለት ግን ይችላል፡፡ ያም ሆኖ ኢትዮጵያውያን ጀግና አትሌቶች በውድድሩን መካተታቸውን በመንገድ ላይ የተመለከቱ አንዳንድ ወንድሞች መኪኖቻቸውን እያቆሙና ስራቸውን እያሽቀነጠሩ ቀዝቃዛ ውሃ ይዘው አብረዋቸው በመሮጥ ለተወዳዳሪዎች ሞራል እየሰጡ ሲሮጡ ለተመለከተ ያኮራሉ ልብንም ያባባሉ፡፡ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውድድሩን ሲያጠናቅቁ የታየው የህዝብ ድጋፍ ጭብጨባና ሞራል ደግሞ ከሁሉም በላይ ማንነትን ያደምቃል፡፡ ሃበሻ ሞልቶ በተረፈባት የጅዳ ከተማ ባንዴራ የሚያቀብልም ኢትጵጵያዊም ሆነ አሰራሩ እየተሻሻለ መጥቷል የተባለው ቆንስል መስሪያ ቤት ተወካዮችን ምን ነካቸው? ማለቴ ግን አልቀረም ! አትሌቶች በመንገድ ላይ አይቷቸው አብሮ እየሮጠ የመጣ ወጣት መለሰልኝ "ይህንን መልካም ዜና ለአዲሱ አምባሳደር የሚያደርስ ጠፍቶ እንጅ እሳቸው መገኘታቸው አይቀርም ነበር "ያለኝ ወጣት በአትሌቶች ማሸነፍ የተሰማውን ደስታ መግለጽ ቃላት ጠፍቶበት ደስታውን አጫወተኝ ነበር!



ለስምንተኛ ጊዜ በሳውዲ አረቢያ ጅዳ በተደረገው ማራቶን ኬንያ ከካታር ከባህሬን ከሞሮኮ ከፈረንሳይ ከሳውዲ አረቢያ በርካታ አትሌቶች ተሳታፊ እንደ ነበሩ አዘጋጆች ገልጸውልኛል፡፡ አትሌቶችን በመምራት በጅዳው ማራቶን እንዲሳተፉ ያደረጉት ሯጭ ተስፋየ ግርማ ሺፋው በበኩላቸው እሳቸውም ከዚህ በፊት ለሁለት ተካታትይ አመታት የጅዳው ማራቶንን ድልን በመቀዳጀት የመኪና ሺልማት ማግኘታቸውን በከራት አስረድተውኛል፡፡ ስላመጧቸው ወጣት አትሌቶችና ስለተገኘው ድል አነጋግሬያቸው በግል ውድድሩን እንዲሳተፉ የአደረጓቸው አትሌቶች 12 ገልጸዋል፡፡ በወጣቶች የስድስት ኪሎ ሜትር ውድድር አትሌት ሰለሞን ደሴሳና ሃብታሙ ጃለታ አንደኛና ሁለተኛነት በመግባት ድልን መቀዳጀታቸውን ሲታወቅ ከወጣቶች ውድድር ለጥቆ በተደረገው የግማሽ ማራቶን ውድድርም ቶላ ባኔ

አንደኛ ደረጀ ተስፋየ ሁለተኛና ተስፋየ ግርማ በሶስተኛነት በመምራት ከአንድ እስከ  አስር ተከታትለው በመግባት የአረንጓዴው ጎርፍ የተለመደ የኢትዮጵያውያንን ድል በጅዳው ማራቶን አይበገሬነታቸውን አሳይተዋል፡፡



 የጅዳ ማራቶንን ለተከታታይ አመታት ያዘጋጀው ድርጅት የበላይ ሃላፊና ታዋቂውን በሳውዲ የመኪና እሽቅድድም ክብረ ወሰን ባለቤት አብደላህ ባከሽብን በኢትዮጵያውያን ሯጮች ስለተገኘው ድል አነጋ ግሬያቸው ሲመልሱ" ኢትዮጵያን ሯጮች በየአመቱ ይሳተፋሉ የመጀመሪያውን ሽልማት በተደጋጋሚ የሚያገኙት ኢትኦጵያውያን ናቸው፡፡ በእውነቱ ኢትዮጵያን ሯጮች እጅግ በጣም ጎበዞች በመሆናቸው ሁሌም ቢሆን በዚህ በጅዳ ማራቶን ተሳትፏቸው አስደሳች ነው፡፡" ሲሉ ገልጸውልኛል፡፡



 በበነጋው በተደረገው የሽልማት ደማቅ ስነ ስርአት የጅዳ ሃገረ ገዥን ጨምሮ የመንግስት ከፍተኛ ባልስልጣናትና ባለሃብቶች የተገኙ ሲሆን የኢትዮጵያ መንግስት ተወካዮች የሆኑት የጅዳ ቆንስል መስሪያ ቤት ሃላፊዎች አልተገኙም፡፡ ስለውድድሩ በቂ መረጃ የነበራቸው አንዳንድ የቆንስል ባለልጣናት ሌላው ቢቀር መረጃውን በጅዳና አካባቢው የሚገኙ ነዋሪዎች እንዲያውቁት ባለማድረጋቸው የሃገር ኩራት የሆኑት አትሌቶች አሸንፈው ሲገቡ በሃገራቸው መንግስት ተወካዮችና ዜጎቻቸው ለሯጮች ከተገቢ የሞራልና ድጋፍ  አልፎ የሃገራቸው ባንዴራ እንዲያውከበልቡ አለማድረጋቸው ሊታረም የሚገባ ነው ብሎ ማለፉ ካግባባን በዚህ እንለፈው ! ያም ሆኖ በአጋጣሚ ውድድሩን የተከታተሉት ቁጥራቸው ጥቂት ኢትዮጵያውያንና የተለያዩ ሃገራት ስፖርት አፍቃሪ  ታዳሚዎች በኩል የተሰጣቸው ሞራልና ድጋፍ የሚያስደስት ነበር ማለት ይቻላል !

 ለሰሚው  ግራ የሚያጋባውና ከሁሉም የሚገርመው ነገር ቢኖር 12 ያህል ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከሃገር ቤት በግል መጥተው መወዳደራቸውን ከቡድኑ መሪዎችና ከአትሌቶቹ አንደበት ለመገንዘብ ብችልም የውጤታቸውን ዝርዝር በወጣበት በጅዳ ማራቶን አዘጋጆች ድህረ ገጽ አብዛኛው አትሌቶች ዜግነት ታንዛንያን ኬንያን ካታርንና የተባበሩት ኢምሬትን እንደሆነ ይፋ አድርጓል፡፡



http://www.jeddah-marathon.com/2011_results.php
ለውድድሩ አሸናፊዎች የጅዳ አገረ ገዥ አሚር በተገኙበት መኪናን ጨምሮ የገንዘብና የተለያዩ ሽልማቶችን ሲሸለሙ በስነ ስራቱ ላይ ተገኝቸ ያነጋገርኳቸው አትሌቶች የተወዳደሩት በግል ቢሆንም ዜግነታቸው ኢትዮጵያዊ መሆኑን እንጅ የሌላ ሃገር ዜጎች ተብለው በድህረ ገጹ ስለወጡበት ሁኔታ የሚያውቁት እንደሌለ አጫውተውኛል. . . ዛሬ በሰሞነኛ ወጋ ወጌ የአረንጓዴው ጎርፉን



ድል በሳውዲ ስለደገሙት ጀግና አትሌቶች ይህንን ካልኩ ወደ ሌላው ድብቅ እውነት ዝርዝር ጉዳይ ገብቸ ጊዜያችሁን አላጠፋም . . . ደግሞም በእንጥልጥል የተውኩት ጉዳይ አለኝና በዚህኛው አልባዝንም ! ባለፈው መጣጥፌ ወርቅ እናፍስ በለው ሲያልሙ በበሺታ ተቀስፈው በጅዳ ቆንስል መስሪያ ቤት እንዳሉ ያጫወኳችሁ ወገኖቻችን በኩል ደስ የሚያሰኝ ወሬ ሰምቻለሁ ! ለ15 አመታት ቆንስሉ በሃላፊነት የመሩት አምባሳደር ወደ ሃገር ቤት በተሰናበቱ ማግስት የመጡት አዲስ አምባሳደር የኒያ ግፉአን ወገኖቻችን እንግልት ያበቃ ዘንድ የሰሩት መሳካቱን ሰምቻለሁ! አዲሱ አምባሳደር በጀዛን በግፍ ስላለቁት ወገኖች ባዳ ቢሆኑም ችግር ለመቅረፍም እያደረጉት ያለው ጥረትም የሚያበረታታ መሆኑን ከወደ ጅዛን ሰማቻለሁ ! ለሁሉም አዲሱን የምስራችም ሆነ በአደጋ ላይ ያሉ ወገኖችን ለመታደግ ስለተጀመረው ጥረት ባየሁ በሰማሁት ዙሪያ የምለው አይጠፋምና የነገ ሰው ይበለን !

ለዛሬው በዚህ ላብቃ . . .

ቸር ይግጠመን !